







አምስቱ አሰማዳ ምስጢራት

ቅ/ዲዮናስዮስ “ወደላይ አቅጎተጎ እጎለምጎ ያጎ ጊዜ የመለኮትጎ ነገር ከሚናገሩ መጻሕፍት ዕውቀት ይገልጥልናል ከእነርሱም የቅድስት ሥላሴጎ ስም በመጥራት ዐዋቂዎች እጎሆናለጎ ይእውም ማመናችጎ ነው” **ሃይ.አበው ምዕ.10፡1**

አዘጋጅ፡- ኢዮብ ዘገነተ ጽጌ

ለምን እንማራለን

- **1.በጽኑ ዓለት ላይ ለመመሥረት ነው**

ማቴ16፡18 “አንተ ኬኩሐ(አንተ ጴጥሮስ) ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እመሠርታታለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏም”

ማቴ7፡24 “ስለዚህ ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው በዓለት ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም”

- **2ኛ.የምናምነው ስለሆነ ነው**
- **አማኒ(አማኝ)- Theist** ለመባል መሠረታዊው (ቀዳሚው) የመዳን በር በአምስቱ አዕማደ ምስጢራት ላይ ካለው እምነት ላይ መሠረት ያደረገ ነው::
- **ቅ/ዲዮናስዮስ “ወደላይ አቅንተን እንለምን ያን ጊዜ የመለኮትን ነገር ከሚናገሩ መጻሕፍት ዕውቀት ይገልጥልናል ከእነርሱም የቅድስት ሥላሴን ስም በመጥራት ዐዋቂዎች እንሆናለን ይኸውም ማመናችን ነው” (ሃይ.አበው ምዕ10፡1)**
- ዮሐ 6፡ ስምዖን ጴጥሮስ ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤
  69 እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም ብሎ መለሰለት።

“እኛ በዓይነ ልቡናችን ብናየው በረቂቅ አዕምሩአችን ብናስተውለው የክርስቲያን ሃይማኖት ታላቅ ነው” ሃይ.አበው ዘቅዱስ ቆዝሞስ

ለምሳሌ፡- የምንጸልየው ጸሎተ ሃይማኖት አምስቱ አዕማደ ምስጢራት ናቸው

- ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ ልጅ በሚሆን በእንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን።
- ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፤ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፤ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ፤ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል። ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም፤በሰማይም ያለ በምድርም ያለ።
- ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ። ሰው ሆኖ በጲንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ ታመመ ሞተ ተቀበረ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ።
- በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ዳግመኛም በሕያዋንንና በሙታንንም ለመፍረድ ይመጣል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።
- በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን እርሱም ጌታ ከአብ የሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለት እናመሰግነዋለን እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ።
- ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን። ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን። የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን። የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን።

3ኛ.የድኅነታችን አካል ስለሆነ ነው

1ኛጢሞ 3፡15 “ከሕጻንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ዐውቀሃል”

1ኛ ጢሞ 6፡3” እነዚህን አስተምርና ምከር ማንም ልዩ ትምህርት የሚያስተምር ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት”

እልመስጦአግያ “ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወደውን ጣውቁ ዘንድ የድኅነታችሁንም ምሥጢር ታስተውሉ ዘንድ” ሃይ.አበው 4፡6

- **4ኛ.ከአሕዛብ ከመናፍቃን ከተለያዩ.. ለሚነሱብን ጥያቄዎች መልስ መስጠት እንችል ዘንድ ነው**

1ኛጴጥ 3፡15 “በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ ነገር ግን በየዋኅነት ና በፍርሃት ይሁን”

የሃይማኖት ትምህርት

- 1ኛ.ዕውቀታዊ (Scholastic) ነው
- 2ኛ.ምስጢራዊ (mystical)ነው
- 3ኛ.ወደ ሱታፌ አምላክ (Theosis) የሚያደርስ ነው
- 4ኛ.ሰዎች የማሰብ መጠን(Intellectual capacity) የማይደርስበት ነው
- 5ኛ.በአባቶች አስተምህሮ ሕይወትና ጽሑፎች(Patristic) የተመሳከረ ነው
- 6ኛ.መጽሐፍ ቅዱሳዊ(biblical) ነው
- 7ኛ.በአንጽሖ መንፈስ (catharsis) የሚረዱት ነው

የሃይማኖት መመሪያዎች

- **ዶግማ ቀኖና ትውፊት**
- **እነዚህ የሃይማኖታችን መሠረቶችና በአምልኮት በሥርዓት በአስተምህሮ ቤ/ክ እንደ ምሰሶ ጸንታ እንድትቆይ ያደረጉአት ፤ ምዕመናንም የምንመራባቸው መሠረቶቻችን ናቸው**
- መናፍቃንን እስከ መወገዝ የሚያደርሳቸው ከነዚህ መሠረቶች እንውጣ ባሉ ጊዜ ነው
- በሃይማኖተ አበው
- **የዶግማ :- “የእግዚአብሔር ልጅ የነሳው ሥጋ ከሰማይ የተገኘ ነው ሥጋውንም ከሰማይ ይዞ መጣ የሚል ቢኖር ውጉዝ ይሁን” (ምዕ.59 ክ.8 ቁ.9)**

የሃይማኖት መመሪያዎች

- **የቀኖና፡-** “የቀና ሃይማኖት ያለው ኤጲስ ቆጶስ የለም ቄስም ዲያቆንም የለም የሚል ቢኖር በዚህም አርቶዶክሳዊት ሃይማኖት አልፋለች የሚል ዳግመኛም ጥምቀት የለም የመድኃኒታችን የክርስቶስ ሥጋው ደሙ የለም የሚል ቢኖር ውጉዝ ይሁን”
  ምዕ.59 ክ.8 ቁ.9
- **ትውፊት ፡-** የአርጌንስ ውግዘት

የሃይማኖት መመሪያዎች

- **ዶግማ (Dogma)፡-** ዶክይን ከሚለው የግሪክ (የጽርእ) ቃል የተገኘ ሲሆን በጥሬው አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ አዋጅ ማለት ቢኾንም በምሥጢራዊ ማለትም እንደ ቤተ ክርስቲያን አተረጓገም ግን **የማይለወጥ፣ የማይቀየር፣ የማይሻሻል፣ የማያረጅ መሠረተ እምነት** ማለት ነው፡፡

- በመኾኑም **ዶግማ የተደነገገ ሳይኾን የተገለጠ** ነው፡፡ መገኛውም እግዚአብሔር ነው፡፡ ከሰው ሊፈጠር አይችልም፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እውነት ነው፡፡ በማኝኛውም አካል (በሲኖዶስም ጭምር)፣ በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛውም ኹኔታ (በሞትም በሕይወትም) የማይለወጥ ማንነት አለው፡፡
- ዶግማ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርተ ሃይማኖት ነው ብለናል፡፡ ስለ ቅድስት ሥላሴ፣ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ፣ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ስለ ምሥጢረ ቁርባን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ክብረ ድንግል ማርያምና ክብረ ቅዱሳን የምንማረው ነው እንጂ ማናችንም ልናሻሽለው አንችልም፡፡

- እንኳንስ አንድ ግለሰብ ይቅርና ሲኖዶስም ቢኾን አለመለወጡን፣ አለመፋለሱን መርምሮ ሃይማኖታችን ይህ ነው በማለት ያሳውቃል እንጂ መጨመር ወይም መቀነስ አይችልም።
- ሐዋሪያው **ቅዱስ ጳውሎስ**፡- **‹‹ነገር ግን (ሐሳባችንን ቀይረን) እኛ ብንኾን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችኁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን የሚሰብክላችኁ የተረገመ ይኹን››** ያለውም ስለዚኹ ነው **/ገላ.1፡8/**

የሃይማኖት መመሪያዎች

- **ቀኖና(Canon)** :- ማለት ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ፍርድ፣ ቅጣት፣ መጠን፣ ልክ ማለት ነው። በግሪኩ ካኖን ሲባል በዕብራይስጡ ቃኒህ ይሉታል። ይኸውም አንድን ነገር ለመለካት፣ ለመመዘን፣ ትክክል መኾኑንና አለመኾኑን ለመለየት፣ መጠኑን ለማወቅ የሚያገለግል መለኪያ ወይም መስፈርት ነው።
- ቀኖና በዋናነት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያንም ቀኖና የሚለውን ቃል ስትጠቀም የመጻሕፍቶቿን ዝርዝር፣ የሥርዓተ አምልኮቷን አፈጻጸም፣ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን አፈጻጸም፣ የአንድ ክርስቲያን ሥነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት የሚገልጠውን ሥርዓት፣ ሕግና ደንብን ያመለክታል።
-

የሃይማኖት መመሪያዎች

- **ሥልጣን ባለው አካል (በቅዱሳን ጳጳሳት ጉባኤ)** የሚደነገግ፣ የሚተገበር፣ የሚሻሻል ነው። ሲደነገግም ሲሻሻልም በግለሰቦች የግል ፍላጐት ወይም ፈቃድ የሚደነገግ ወይም የሚሻሻል አይደለም።
- **ሃይማኖታዊ ይዘት አለው**። ምክንያቱም ዓላማው ሰውን ሁሉ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ማፍለስ ስለሆነ ቄሣራዊ ይዘት የለውም። ቢኖርም እንኳን አንድ ክርስቲያን በዚህ ምድር የሚኖረው ቆይታ ከሰማያዊ ሕይወቱ ጋር ሳይጣረስበት እንዴት መኖር እንዳለበት የሚያስረዳ ነው።
- የሰው ልጅ ከሚችለው በላይ ሸክምን አይጭንም፤ **“ሸክሜ ቀሊል ነው”** እንዲል /ማቴ.11፡29/።
- **የሸላሚነትና የቀጪነት ሥልጣን አለው**። ቄሣራዊ ሕግ የሸላሚነት ይዘት የለውም። በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ግን ለምሳሌ ተጋድሎአቸውን በድል ያጠናቀቁት ክርስቲያኖች ቀን ተለይቶላቸው፣ ታቦት ተቀርጾላቸው በምእመናን ዘንድ ክብርን እስከ ማግኘት ይደርሳሉ። በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ የዘለዓለም አክሊል ዘውድ አለው።
- **የአምልኮ ይዘት አለው**። በውስጡ ጸም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት እና የመሳሰሉትን ኹሉ ያካትታል።

የሃይማኖት መመሪያዎች

- **የመመዘን ጠባይ አለው**፡፡ ለምሳሌ የቃየን መሥዋዕት ያልሰመረችው መሥዋዕት ስላላቀረበ ሳይኾን በሕጉ መሠረት አሰስ ገሰስ ኾኖ ስለተገኘ ነው /ዘፍ.4/፡፡
- በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ የተደነገገ አይደለም፡፡
- **ሰዎችን ደስ ለማሰኘት አይወጣም**፤ የሚወጣው እግዚአብሔር ደስ ለማሰኘት ብቻ ነው፡፡ “ለዓለም ከሚመች ከንቱ ልፍለፋ ራቅ” እንዲል ለዓለም የሚመች ቀኖና አይወጣም፡፡ ቀኖና የሚወጣው የምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያድግና ምእመናን በሚኖሩበት ማኅበረ ሰብእ ውስጥ አርአያ እንዲኾኑ ነው፡፡
- **አንጻራዊ ጽድቅ ስለሌለ አንጻራዊ ቀኖናም የለም**፡፡ ጥቁሩን ጥቁር ነጩንም ነጭ የሚል እንጂ የተድበሰበሰ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አታወጣም፡፡

◉ቀኖና በመጽሐፍ ቅዱስ

- ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በሥርዓትና በቀኖና ትመራ ዘንድ አዝዘዋል። **‹‹ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን።።›› (2ኛተሰ 3፤6) ብለዋል።**
- በተጨማሪም ለሥርዓት ዘብ መቆም እንደሚገባ ሲያመለክቱ ‹‹ወንድሞች ሆይ ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገስጹአቸው።።›› ብለዋል (2ኛ ተሰ 5፤14፣ 1ኛ ቆሮ 14፤40)።
- ከአይሁድ ወደ ክርስትና የመጡ ወገኖች ከአሕዛብ ወደ ክርስትና የገቡትን የሙሴን ሥርዓት ካልፈጸማችሁ (ግዝረትን፣ የመንጻት ጥምቀትን . . .) አትድኑም በማለት በቤተ ክርስቲያን ውዝግብ አስነሥተው ስለነበር ሐዋርያት ችግሩን ለመፍታት በኢየሩሳሌም የመጀመርያውን ጉባኤ (ሲኖዶስ) አድርገዋል።
- በችግሩም ዙርያ ከተነጋገሩ በኋላ 3 ቀኖናዎችን ደንግገዋል። እነዚህም በሐዋ. ሥራ 15፤29 ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም ኤጲስ ቆጶሳትና ዲያቆናት ለአገልግሎቱና ለሥልጣኑ ማሟላት ያለባቸውን መሥፈርቶች ዘርዝረዋል። መሥፈርቶቹም ቀኖና (ሥርዓት) እንደሆኑ እንረዳለን (1ኛ ጢሞ 3፤2-13)።

የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ምንጮች

- **የሐዋርያት ሲኖዶስ፡-** እነዚህ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጻሕፍት ብላ በምትቀበላቸው ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ስለ ቅዳሴ፣ ወደ ምሥራቅ ዞሮ ስለመጸለይ፣ በሰንበት፣ ረቡዕ፣ ዓርብና እና በተለያዩ በዓላት የሚጸለዩ ጸሎቶች፣ ስለ ሥርዓተ ክህነት፣ እንዲሁም ስለ አንድ ምእመን ክርስቲያናዊ ሥነምግባር . . . ወዘተ የሚገልጡ ቀኖናዎች ናቸው፡፡

- **ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት**፡- እነዚህም በ3ቱ ጉባኤያት ማለትም በጉባኤ ኒቂያ፣ በጉባኤ ቍስጥንጥንያ፣ በጉባኤ ኤፌሶን ላይ የተወሰኑ የተለያዩ ሥርዓቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ቀኖናት በሁሉም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነትና ተፈጻሚነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- **ብሔራውያን ጉባኤያት (የውስጥ ጉባኤያት**)፡- እነዚህ ደግሞ ዓለም አቀፋዊ ሳይሆኑ በየሀገሩ ወይም በየአካባቢው በሚደረጉ ሲኖዶሶች የተወሰኑ ቀኖናዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የዕንቆራ ጉባኤ፣ የቅርጣግና ጉባኤ፣ የሎዶቅያ ጉባኤ፣ የጋንግራ ጉባኤ፣ . . . ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያው 3ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ዘመን ምእመናን በጾም ወቅት ዓሣ እንዳይመገቡ ተወስኗል፡፡ እነዚህ ቀኖናት በዚያ ሀገር ወይም አካባቢ ውስጥ ብቻ ተፈጻሚነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

- **የአበው ውሳኔ፡-** የተለያዩ ቅዱሳን አበው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው የወሰኗቸው ቀኖናዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ እንደ ቅዱስ አቡሊደስ (በምሕጻረ ቃል “በደስ” ይባላል)፣ የቅዱስ ባስልዮስ በጋብቻ በክህነትና በምንኩስና ላይ የሠራቸው ቀኖናዎችን (“ባስ”)፣ . . . የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ጥቅሞች

- **የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሥርዓት እንዲኖረው ያደርጋል።**
- የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ይጠብቃል። ለምሳሌ ውዝግቦችን በመፍታት እና በሁሉም ቦታ ተመሳሳይ የሆነ አገልግሎትና ሥርዓት እንዲኖር ያግዛል (ዮሐ 15፤1-29)
- በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ካልሆነው መለኪያ (Standard) በመሆን ያገለግላል።
-

- **ቅዱስ ትውፊት (Holy Tradition)፡-**
  በሰዋሰዋዊ ዘይቤው ሲፈታ፥ ትወፊት ማለት ስጦታ፣ ልማድ፣ ትምህርት፣ ወግ፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ ሥርዓት፣ ከጥንት ከአበው ሲያያዝ ሲወርድ፥ ቃል በቃል ሲነገር የመጣ ማለት ነው /አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ገጽ፣ 397/

- **በግሪክ(በጽርዕ)** “**ፓራዶሲስ**” ይባላል፤ አንድን ነገር እጅ በእጅ ለሌላ ሰው ማስረከብን ወይም ማቀበልንም ያመለክታል። ዕብራውያን ደግሞ “**ማሳር - ማቀበል**” እና “ቂብል - መቀበል” የሚሉ ቃላትን ይጠቀማሉ።

ቅዱስ ትውፊት (HOLY TRADITION)፡-

- ቤተ ክርስቲያን ለቃሉ የሚከተለውን ትርጉም ሰጥታዋለች፡፡ **ትውፊት ማለት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በጠቅላላ በአበው፣ በነቢያት፣ በሐዋርያት፣ በጳጳሳት፣ በሊቃውንት፣ በካህናት በኩል የሚያስተላልፈው ሕያው (ሕይወትን የሚሰጥ) ቃል ማለት ነው፡፡ ይኽ ሕያው ቃል ቀደምት አበው ከእግዚአብሔር የተቀበሉትና ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፉት፥ ቤተ ክርስቲያንም በየጊዜው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የምትጠቀምበት ሕያው ትምህርት ነው፡፡**

- እንደ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ፥ እግዚአብሔር ከፍጥረት መዠመሪያ አንሥቶ በጽሑፍም ያለ ጽሑፍም የገለጠውን እውነት የምናገኘው በቅዱስ ትውፊት ውስጥ ነው፡፡ በመኾኑም የተጻፈውና ያልተጻፈው ቅዱስ ትውፊት ለድኅነታችን የሚኾን የእግዚአብሔርን መገለጥ የያዘ ስለኾነ አስፈላጊ ነው፡፡

ቅዱስ ትውፊት (HOLY TRADITION)፡-

- ትውፊት ሲባል ስላለፈ ነገር ብቻ የሚናገር፥ ነገር ግን በአኹኑ ሰዓት ምንም ሕይወት እንደሌለው ተደርጐ የሚታሰብ አይደለም፡፡

- አኹንም ሕይወት ያለው ብቻ ሳይኾን ሕይወትንም የሚሰጥ ነው፡፡ ለምሳሌ **መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱስ ትውፊት አንድ አካል ነው(የተጻፈ ትውፊት ነው)፡፡** ነገር ግን ስላለፈው ነገር ብቻ የሚናገር አይደለም፡፡ አኹንም ሕይወትን የሚሰጥ ነው፡፡ ስለዚኽ ትውፊትን መቀበል ያለፈውን ነገር የመጠበቅ ጉዳይ ብቻ አይደለም ማለት ነው፤ የሕይወት ጉዳይ እንጂ፡፡ በሌላ አነጋገር የምንጠብቀው የሕይወት ጉዳይ እንደኾነ ስለሚገባን ነው ማለት ነው፡፡

- **እግዚአብሔር በዚኹ ቅዱስ ትውፊት ሲናገር ስላለፈው ነገር ብቻ ሳይኾን ስለአኹኑም ስለሚመጣውም ዘለዓለማዊ ሕይወት ነው፡፡ ትውፊትን ቅዱስ ብለን መጥራታችንም የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ስለማይለየው፥ አንድም ከክርስቶስና ክርስቶስ አድሮባቸው ከሚኖር ከቅዱሳን የተገኘ ስለሆነ ነው፡፡**

ቅዱስ ትውፊት (HOLY TRADITION)፡-

- እንደ ምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን (ካቶሊክ) ትርጉም ቅዱስ ትውፊት ማለት ያልተጻፈ ነገር እና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍን ብቻ የያዘ ነው /J.N.D. Kelly, Early Christian Doctrines, pp 30-31/::
- በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ግን ከላይ እንደገለጥነው ቅዱስ ትውፊት የተጻፈውም ያልተጻፈውም ኹሉ የሚያካትት ነው::
- በመኾኑም (ቅዱስ ትውፊት) በውስጡ መጽሐፍ ቅዱስን፣ የአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትን፣ የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትንና ቀኖናትን፣ የሦስቱን ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያትን (ጉባኤ ኒቅያ፣ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ፣ ጉባኤ ኤፌሶን) እና ትእዛዛትን፣ መጻሕፍተ ቅዳሴያትን፣ ገድለ ቅዱሳንን፣ ቅዱሳት ሥዕላትን፣ የቤተ ክርስቲያን አመራርና የሥርዓተ አምልኮ አፈጻጸምን፣ ክርስቲያናዊ የአለባበስ፣ የአነጋገር እንዲኹም የአመጋገብ ሥርዓትን ሌላውንም ኹሉ ያካተተ ነው::

- Georges Florovsky; Bible, Church, Tradition: An Eastern Orthodox View; Vol.I; pp 46

ቅዱስ ትውፊት (HOLY TRADITION)፡-

- ትውፊትን ቁሳዊ፣ ቃላዊና ርእያዊ ብለን በ3 ልንከፍለው እንችላለን፡፡

- **ርእያዊ፡-** ይህም ማለት በመጻሕፍትና በቃል ባይገለጥም በማየት የወረስነውን ያመለክታል፡፡
- ለምሳሌ ፡_በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ የነበረው ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ ፍሎሪነስ ለተባለ ጓደኛው ሲጽፍለት፡-
- ‹‹ ነፍስ እስከማውቅና በሕይወቴ እስኪዋሐደኝ ድረስ በሕፃንነቴ የተማርኩትን አኹን ከምማረው በላይ ወለል ብሎ ይታየኛል፡፡ ቅዱስ ፖሊካርፐስ (የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደቀመዝሙር ነው) ሲቀመጥበት የነበረውን ቦታ፣ የትምህርት አሰጣጡ ዘዴ፣ እንዴት ይገባና ይወጣ እንደነበር፣ ክርስቲያናዊ ሕይወቱና የሰውነቱ መልክዕ፣ ለምእመናን ያስተማረውን ትምህርት፣ ከወንጌላዊ ዮሐንስና ከሌሎች ጌታችንን በዓይን ካዩት ደቀ መዛሙርት ጋር ስለነበረው ትውውቅ፣ ትምህርታቸውን እንዴት ያስታውሰው እንደነበር፣ ስለ ጌታ ከእነርሱ ምን እንደሰማ፣ ጌታችን ያደረጋቸውን ተአምራትና ያስተማረውን ትምህርት ይኸንና ይኸን የመሰለ ኹሉ ቅዱስ ፖሊካርፐስ ከቃሉ አገልጋዮችና ምስክሮች እንደምን እንደተቀበለና ለእኛ እንዴት እንዳስተላለፈልን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አዋሕዶም እንዴት እንዳስተማረን አስታውሳለኁ፡፡
- የእግዚአብሔር ቸርነት ረድቶኝ፣ በሕፃንነት አዕምሮዬ እነዚኽን ነገሮች ለመስማትና በወረቀት ሳይኾን በልቤ ጽላት እጽፋቸው ዘንድ ደግሞም ዘወትር አስባቸው ዘንድ እጅግ እጓጓ ነበር ›› በማለት ከቀደሙት አበው ስለተቀበለውና በኑሮ፣ በሕይወት ስለሚገለጡ፣ ግን ደግሞ ያልተጻፉ ትውፊቶች እንዳሉ አብራርቶ የተናገረበት አኳኋንም የትውፊትን ምንነት ፍንትው አድርጎ የሚተረጉምልን ነው //፡፡››

/Fr. Tadros Y. Malaty, Tradition and Orthodoxy, pp 23/

ቅዱስ ትውፊት (HOLY TRADITION)፡-

- **ቃላዊ፡-** ይህ ዓይነቱ ደግሞ በንግግር ከአባቶች ሲተላለፍ የመጣውና እኛ ደግሞ በመስማት የምንቀበለውን ያመለክታል (2ኛ ተሰ 2፤15)።
- **ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ‹‹የትኞቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የትኞቹ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደሆኑ ከቤተክርስቲያን ጠቅቀህ ተማር ›› ብሏል።** ይህም የሚያስረዳን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የመጻሕፍቱን ብዛት ቀኖና ሲሠራለት እውነተኞቹን መጻሕፍት ከሐሰተኞቹ ለመለየት አባቶች የተጠቀሙት ቅዱስ ትውፊትን መሆኑን ነው።
- ለምሳሌ :_**ቅዱስ ሄሬኔዎስ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ አምስት መጻሕፍትን እንደ ጻፈ እነዚህንም መጻሕፍት የሰበሰበው ደቀ መዝሙሩ ቅዱስ ፖሊካርፐስ እንደሆነ ጽፏል፡**። ስለዚህም ቅዱሳን አባቶች ከዚህ ትውፊት በመነሣት **5ቱን የቅዱስ ዮሐንስን** መጻሕፍት በሐዲስ ኪዳን ቀኖና(የመጻሕፍት ዝርዝር) ውስጥ አካተው በሐሰት በእርሱ (በቅዱስ ዮሐንስ) ስም ከተጻፉ መጻሕፍት ለይተዋል።
- በተለያዩ መናፍቃን በቅዱሳን ስም የሚጠሩ ከ50 በላይ የሚሆኑ ወንጌላት ተጽፈው ነበር፤ አባቶችም ከእነዚህ የሐሰት ወንጌላት ለይተው እውነተኞቹን 4 ብቻ በቀኖና አስቀምጠዋል። ለዚህም ነው **ሊቁ አርጌንስ ‹‹በትውፊት ወንጌላት 4 እንደሆኑ እናስተውላለን›› ያለው።**

የክርስቲያናዊ ትውፊት ማረጋገጫዎች

- ቤተ ክርስቲያን እንዲሁ ማንኛውንም ትውፊት ክርስቲያናዊ ነው በማለት አትቀበልም። አንድን ትውፊት እውነተኛ መሆኑን የምታረጋግጥበት የራሷ የሆነ መለኪያ አላት። እነዚህም
- **ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይጣረስ እስከሆነ ድረስ፡-** ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ የትውፊት አንዱ አካል ቢሆንም የመጀመሪያውን ስፍራ ይይዛል። ይህም ካልተጻፈው ቅዱስ ትውፊት ይልቅ በቀላሉ ለስሕተት የማይጋለጥ በመኾኑ ነው። ምክንያቱም በቀኖና አንዴ ተወስኖ (ምን ያህል መጻሕፍት እንዳሉና ይዘታቸው) የቀረበ ነውና። በዚኽም ያልተጻፈው ቅዱስ ትውፊት የሚመዘንበት ሚዛን ነው።
- **ከመሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጋር የማይጋጭ እስከሆነ ድረስ**
- **ከዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ጉባኤያት ውሳኔዎች ጋር የማይጋጭ እስከሆነ ድረስ**
- **ከቅዱሳን አበው አባበሎች ጋር ቅራኔ ሳይኖረው ሲቀር ብቻ ነው።**

ዶግማ

አምስቱ አዕማደ ምስጢራት

- ትምህርተ ሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር የምታደርሰውን ፍኖተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መንገድ) የምናውቅበትና ዘላለማዊ ሕይወትን የምንጎናጸፍበትን “ርትዕት ሃይማኖት” የምንገነዘብበት ነው። ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትን ዶግማ (መሠረተ እምነት) እና ቀኖና (ሥርዓተ ቤተክርስቲያን) ብለው በሁለት ይከፍሉታል።
- የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት መሠረት እንደሆኑ የምታምነውና የምታስተምረው አምስቱ አዕማደ ምስጢራትን ነው። በዚህች የአስተምህሮ ጦማር የአምስቱ አዕማደ ምስጢራት-መግቢያ የመግቢያ ክፍል የሚቀርብ ሲሆን የአንዳንድ ቃላትን ትርጉም በመግለጽ እንጀምራለን።

አዕማድ ምን ማለት ነው

- **አዕማድ(ዐምድ)፡-** “**አዕማድ**” የሚለውም ቃል መገኛው “**አምድ**” የሚለው የግዕዝ ቃል ነው፡፡ “አምድ” የሚለው ቃል የነጠላ ቁጥርን የሚገልፅ ሲሆን “አዕማድ” ሲሆን ደግሞ ብዙ ቁጥርን ይገልፃል፡፡
- ትርጉሙም በቃላዊ ፍቺው ለቤት ሲሆን **ምሰሶ ማለት ነው፡፡** ምሰሶ ቤትን ደግፎ እና አቅንቶ እንደሚይዝ ሁሉ አምስቱ አዕማደ ሚስጥራትም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን አቅንተውና ደግፈው ስለሚይዙ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ዐምድ ለጽሕፈትም ይውላል፡፡
- የገጽ ስፋትንም በመክፈል ለንባብ መመጠኛነት ያገለግላል፡፡ በዚህ ፍቺም ባህርየ ሥላሴን ከልክ አልፈን እንዳንመረምር የተሰጠ ስያሜ ነው፡

አዕማድ ምን ማለት ነው

- **አምድ** በቁሙ ምሰሶ ብለን የምንጠራው እና ቤቱ እንዳይዘም ወይም ወደ አንድ ጎን እንዳያዘነብል፤ ሚዛኑን እና ልኩን ጠብቆ እንዲቆም የሚያደርግ ነው። በአምድ የተሠራ ቤት አይዛባም ያለዓምድ የተሠራ ቤት ግን ይፈርሳል አይጸናም። ቤት በአምድ (በኮለም) እንደሚጸና ሃይማኖትም በእነዚህ አዕማደ ምሥጢራት ተጠቃሎ ይገለጻል፤ ምዕመናንም እነዚህን ምሥጢራት በመማር ጸንተው ይኖራሉ። እንደዚህም ሁሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አዕማድ የተባሉ ምሥጢራት ይዞ የተገኘ ሰው ልቡናው በፍቅረ እግዚአብሔር በተስፋ መንግስተ ሰማያት ይጸናል። እነዚህን አምስቱን እምነታት ሳይዝ የተገኘ ልቡናው በፍቅረ እግዚአብሔር በተስፋ መንግስተ ሰማያት አይጸናም።
- **“ሁሉም ነገር ድጋፍ ያስፈልገዋል”** የሚለው ሃሳብ ለቤቶች ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባለፈ ለብዙ ነገሮች ያገለግላል። ብዙ **የፍልስፍና ሊቃውንት ሰዎች** ሁሉ ህይወታቸው በተገቢው መንገድ ለመምራት ሲሉ የሚቀበሏቸው መሰረታዊ እምነቶች (**fundamental beliefs**) እንዳሉ ይናገራሉ። በዓለም ላይ ከፍተኛ ህዝብ ይከተላቸዋል የሚባሉት ሃይማኖቶችም ሳይቀሩ መሰረታዊ እምነት የሚሏቸው አሏቸው።
- ለአብነትያህል፡- በእስልምናው ሃይማኖት አምስቱ የእስልምና መሰረቶች (The Five Pillars of Islam) ሲኖሩ በቡድሂዝም እምነት ደግሞ አራቱ እውነታዎች (The Four Noble Truths) ይገኛሉ።


አዕማድ ምን ማለት ነው

- በቅድስት ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ ምሰሶዎች አንድን ቤት ደግፈው እንደሚይዙት ሁሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትንም ቀጥ አድርገው የሚይዙ ምሰሶዎች አምስቱ አዕማደ ምስጢራት ናቸው።
- የቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚያስተምሩት ከሆነ አንድ ሰው አምስቱን አዕማደ ምስጢራት በጥንቃቄ ካወቀ የኑፋቄ ማዕበል አይጥለውም። ከእምነቱም አይናወጽም። በህይወቱ የተለያዩ መከራዎች ቢመጡበትም በእነዚህ ትምህርቶች በኩል ራሱን ያፀናል።
- እነዚህን አዕማድ ያላወቅ በሙሉ ልቡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ነኝ ማለት አይችልም። በዚህም ምክንያት እነዚህን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

ለምን ምስጢር ተባሉ

- **ምስጢር፡**- ማለት “**አመስጠረ(ሰጠረ)**” ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን **ድብቅ ስውር ሸሸግ ረቂቅ** ማለት ነው፡፡
- **ምስጢር** ማለት የማናውቀው ያልተነገረ ማለት ሳይሆን ተነግሮ ተጽፎ ነገር ግን መርምረን ፈትሸን ተርጉመን የማንደርስበት ማለት ነው፡፡
- በተለይም አምላካዊ ምስጢር **Unknowable (የማይታወቅ የማይመረመር) Incommunicable(የማይቀርቡትና የማያገኙት) Transcendent(ረቂቅና ርሑቅ) ነው፡፡**
- **አባ ሕርያቆስ** “ይህንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ ተሰውሮ ወደላይ ወጥቶ የሕያው መሰወሪያ የሆነውን ሊገልጥ ይወዳል ከነደ እሳትነቱ የተነሣ ይፈራል ከአየራት ከሩባቸው ሩብ አይደርስም ...አቅቶት ወደቀደመ አኗኗር ይመለሳል”

- **ቅ/ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ** “Real/Perfect Knowledge of God is not to be found in the created world .now the divine nature as it is in itself ,according to its essence ,transcends every act of comprehensive knowledge and cannot be approached or attained by our speculation”
- “ፍጹም የሆነ እግዚአብሔርን ማወቅ በዓለመ ፍጡራን ሊኖር አይችልም እግዚአብሔር በባሕርዩ በሰው አዕምሮ (ዕውቀት) ከመጠቅለል በላይ ነውና የእኛ መላ ምቶችም እርሱን ሊቀርቡና ሊገልጹ አይችሉም” (Johannes Quasten,Patrology Volume III,254-296)



- **አባ ሕርያቆስ** “አሁንም ገናንነቱን አንመርምር ጥልቅነቱንም አንጠናቀቅ የገናንነቱን መጠን ለማመስገን የነቢያትና የሐዋርያት አንደበት የማይቻለው ነው” **(ቅዳሴ ማርያም ቁ.87)**

- **ምስጢረ ሥላሴን በተገለጠልን መጠን እናቀዋለን መርምረን ግን አንደርስበትም። “ሥላሴ አንድም ሦስትም ናቸው” እንላለን ነገር ግን እንደ ቁጥር ሕግ መርምረን የምንደርስበት አይደለም።**

- **ቅ/ባስልዎስ ለወንድሙ ለቅ/ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ “ከመከፈል ከመቆጠር ውጪ ናቸው ማለት አንድ ሦስት ይባላሉ እንጂ አንድ ሁለት አይባሉም ቅዱስ ባስልዎስ ለሥጋ ወንድሙ ወንድሜ ሆይ አንድነት በመለየት መለየትም በአንድነት አሉ ብንል አታድንቅ ይህ ከአዕምሮ በላይ ነው ብሎ እንደነገረው” ሃይ.አበው ዘዮሐንስ ምዕ113**

ለምን ምስጢራት ተባሉ?

- <u>አንድ</u>፡ **ረቂቅ እና ስውር ስለሆነው አምላክ የሚናገሩ አስተምህሮቶች ስለሆኑ ነው።**
- የእግዚአብሔርን የአንድነትና የሦስትነት ነገር፣ ቀጥሎ ከሦስቱ አካላት አንዱ ሰው የመሆኑ ነገር፣ እንዲሁም ሰው ከእግዚአብሔር በመንፈስ የመወለዱን ነገር፣ ደግሞም ሰው የሆነውን አምላክ ሥጋውን በመብላትና ደሙን በመጠጣት በእግዚአብሔር መንግስት ለዘለአለም ሕያው ሆኖ የመኖርን ነገርና በመጨረሻም ሰው ለዘላለማዊው ህይወት ወይም ሞት በማይበሰብስ አዲስ አካል እንደገና የመነሳቱን ነገር የሚያስረዳ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ትምህርት የሚያስረዱ በመሆኑ ነው።

- **ሁለት፡ ትምህርቶቹን በሥጋዊ ጥበብ ለመረዳት የማይቻል በመሆኑ ነው።**
- ትምህርቱና እውቀቱ እንደሥጋዊ ትምህርትና እውቀት ተፅፎ የሚቀርብና ተነቦ የሚጠና፣ በሥጋዊው ቁሳቁስ ግዙፍ ማስረጃነት እየተደገፈ የሚሰጥ ሳይሆን
- በአንድ ወገን ከሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ልቦና በእውነተኛ አምልኮ ፈልቆ የሚናገሩትና የሚያስተምሩት፣ በሌላው ወገን ደግሞ በእውነተኛ ፍላጎት በተመሰረት ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ልቦና ሆነው የሚሰሙትና የሚማሩት ረቂቅ የእግዚአብሔር ነገር ስለሆነ ነው።

- <u>ሦስት</u>፡ **ቤተክርስቲያን ለአማንያን ብቻ የምትነግረው እና የምታስተምረው በመሆኑ ነው።**

- ለማያምኑ የማይገለጥ፣ ለሚያምኑ ግን በእውነተኛው መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ የእውቀት ቁልፍ ከፍተው በዚያው በፍፁም ብርሃን ካዩት በኋላ አክብረው የሚጠብቁት “የማይጠፋ እንቁ” በመሆኑ ነው።
- (ማቴ. 7፡6፣ ማቴ. 13፡11)

ምስጢረ ሥላሴ- ምስጢር የተባለው

- ከአብ የወልድ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ መስረጽ በእጹብ ይወሰናል እንጂ እንዲህ ነው ተብሎ አይነገርም ከሕሊና ሁሉ በላይ ነው አይመረመርም
- **ቅ/ዲዮናስዮስ** “**አብ ብርሃን ነው ከአብ የተወለደ ቃል ወልድም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው እንዲሁም ከአብ የሠረጸ መንፈስ ቅዱስም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው ከአብ የወልድ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ መስረጽ በእጹብ ይወሰናል እንጂ እንዲህ ነው ተብሎ አይነገርም**” ሃይ.አበው ምዕ.10 ቁ.12
- ቅ/ጎርጎ.ገባሬ.ተ “**ከሰው ባሕርይ ጋር አይመሳሰልምና ልደቱም እንደ ሰው ልደት አይደለምና ረቂቅ ምሥጢር ነው አይመረመርም** ”ሃይ.አበው 13፡12
- ማቴ11፡27 “አብ ሊገልጥለት ካለው በቀር ወልድን የሚያውቀው የለም ወልድ ሊገልጥለት ካልወደደው በቀር አብን የሚያውቀው ማንም የለም”

- 1ኛ ቆሮ 12፡3 “መንፈስ ቅዱስ ካልገለጠለት በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው የሚል አንድስኳን የለም”

- ዮሐ1፡14 “ለአባቱ አንድ እንደሆነ ልጅ ያለውን ክብር አየን”
- (መልሶ ደግሞ) ዮሐ1፡18 “እግዚአብሔርንስ ያየው አንድስ እንኳን የለም በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ ተረከልን”

- **ቅ/ጎርጎ ገባሬ ተአምር “ ይህን ምስጢር ያውቅ ዘንድ ለሰው ቢገባው ኖሮስ አንድነቱን ሦስትነቱን የተናገረ ወንጌላዊ ዮሐንስ እግዚአብሔርንስ ፈጽሞ ያየው የለም ባላለም ነበር ማንም ፈጽሞ የማያየውን በማን እንመስለዋለን ከአብ የተወለደውን ልደትስ ዛሬ እናውቅ ዘንድ እንደምን እንመረምራለን”** ሃይ.አበው 13፡17

- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ምስጢረ ሥላሴ አይረዳውም ነበር በእመቤታችን ሥዕል ፊት እየተንከባለለ ይማጸን ነበር

- አባ ጊዮርጊስ “የአንተን ምስጢር የባሕርይ አባትህን ምስጢር የሚያውቅ መንፈስ ይምጣ የአንተን ትእዛዝ ከአንተ ጋር ትክክል የሆነውንም አባትህን ትእዛዝ ለመሥራት እንዲያበረታታኝ አብን ካንተና ከመንፈስ ቅዱስ በቀር በባሕርይ የሚያውቀው የለምና”

- **ምስጢረ ሥላሴን እስከተገለጥልን ድረስ የምናውቀው እንጂ ከተገለጠው አልፈን ልንመረምረው የምንችል አይደለም**
- ለምሳሌ፡- **ቅ/ዮሐንስ ዘአንጾኪያ “የሥላሴ ምስጢር በአካል ይለያል በመለኮት አይለይም ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ስግደት እንዲገባ እናስተምራለን ”** ሃይ.አበው 90፡6
- ለዚህም ነው ቤ/ክ በሥዕላቶች “*ሥዕለ ሥላሴን*” ሰው በሚረዳው መልኩ የምትገልጸው ! የሥዕሉ መግለጫ ግን ፊታቸው እርጅናቸው አካላቸው ዓይናቸው..ያ ነው ለማለት ሳይሆን በመጻሕፍት የተጻፉትን ምስጢራት በሰውኛ አረዳድ ለማስገንዘብ ነው፡፡


ሠሉስ
ቅዱስ
ሠዓሊ ዘሪሁን ገ/ወልድ

- ሦስት መሆናቸው - **የአካል የግብር** ሦስትነታቸውን
- በአንድ ዙፋን ተቀምጠው አንድ ዓለም መያዛቸው - በባሕርይ በአገዛዝ በሥልጣን አንድ መሆናቸውን
- **ሽማግሌነታቸው** - ከፍጥረት አስቀድመው የነበሩ መሆናቸውን
- **የብርሃን ክበባቸው-** በባሕርያቸው ቅዱስ ንጹሕ ስለሆኑ
- **በእሳት ወላፈን መታየታቸው-** ባሕርያቸው የማይመረመር
- ደመና- ግሩም ነው እነርሱም ግሩማን ናቸውና
- ደመና - ብሩህ ነው እነሱም ብርሃናዊ ናቸውና
- ደመና- ፈጣን ነው እነሱም ለረድኤት የፈጠኑ ናቸውና

ምስጢረ ሥጋዌ ምስጢር የተባለው

- አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ረቂቁ ገዘፈ ግዙፉ ረቀቀ ምልኡ ተወሰነ የሚወሰነው በሁሉ ምሉዕ ሆነ የማይዳሰሰው ተዳሰሰ የሚዳሰሰው እሳታዊ ሆነ ማለት ምስጢር ነው
- ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ተዋሕዶ፡ሥጋዌ ተፈጸመ በድንግልናም ተጸንሶ በድንግልና ተወለደ ማለት ማይመረመር ረቂቅ ነው
- ኢሳ 9፡6 “ድንቅ መካር ኃያል የዘላለም አባት የሰላም አለቃ”
- ውዳሴ ማርያም “መንክር ወሊዶታ ዘኢይትነገር”
- ቅ/ባስልዮስ “መንክር ድንቅ የሚባለው የማይመረመር ሥራ ነው የማይመረመረው ግብር ከፍጡር ባሕርይ በላይ ነው በመመርመርም ሊደረስበት የማይችል ነው “

- ቅ/ጎርጎርዮስ **“ይህ ልደት በማይመረመር በማይነገር ድንቅ በሚሆን ምሥጢር ተደረገ የሰው ልቡና እንዴት እንደ ሆነ ልደቱን ሊያውቅ አይችልም ዕውቀትን ስለ እርሱ ብቻ እንተው እንጂ እንደ ሕጻናት ወተት ጠብቶ በየጥቂቱ አደገ ከኃጢአት ብቻ በቀር በሥራው ሁሉ መሰለን ሰው ከሆነም በኋላ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኖ በተዋሐደው ተዋሕዶ ጸንቶ ኖረ በሦስት አካላት የአካል አራተኛ የባሕርይ ሁለተኛ አልጨመረም”(ግብረ ሃይማኖት)**
- ቅ/ኤፍሬም “ከሕሊናት ሁሉ የራቀ ለዚህ ድንቅ ምሥጢር አንክሮ ይገባል ምድራዊት ሴት ሰው የሆነ እግዚአብሔር ቃልን ወለደችው ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው እርሱም እናቱን ፈጠረ ከርሷም እርሱ የፈጠረውን ሥጋ ተዋሐደ” ሃይ.አበው 47፡2

- ብዙ መናፍቃን ሥላሴና ሥጋዌ ስላልተረዱ ጠፍተው ቀርተዋል
- ንስጥሮስ - ቃል በሥጋ አደረበት / ሁለት ባሕርይ
- አውጣኪ - ሥጋ ቃልን ዋጠው (መጠጠው)
- ፎጢኖስ- የወልድ ሕልውና ከማርያም ወዲህ
- ማኒና ዋሊጦን - በምትሐት ሰው ሆነ
- አቡሊናርዮስ- ቃል ከእመቤታችን ነፍስን አልነሳም
- - ሥጋን ከሰማይ ይዞ መጣ
- ፕሮቴስታንት - ክርስቶስን ሰው በመሆኑ ከአብ እንዳነሰ፤ ዛሬም ይለምንልናል የሚሉ
- ኤፌ 3፤6 **“ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ ተሰጠ”**

የሥጋዌ(የተዋሕዶ) አስደናቂነቱ

- ፈጣሪ በተዋሕዶ ሰው መሆኑ
- በ15 ዓመት ብላቴና ዘንድ ተጸንሶ መወለዱ
- እመቤታችን ጌታዋን በድንግልና ጸንሳ መውለዷ
- ያለ ዘርዕ ያለወንድ ፈቃድ መውለዷ
- ከተዋሕዶ በኋላ ገዚና ተገዚ አለመኖር
- አምላክ በየጥቂቱ ማደጉ
- አምላክ በፍጥረታዊት እናቱ መታቀፉ
- አምላክ ሆኖ ሣለ ስለ ሰው ፍቅር ሕማምና ሞት መቀበሉ
- ከተዋሕዶ በኋላ ፍጡር አለመባሉ
- ሕግ ተፈጥሮአዊ ሕግ መጽሐፋዊን መፈጸሙ

ምስጢረ ጥምቀት ምስጢር የተባለው

- ግዙፉ ከረቂቅ መወለዱ በሚታይ ውኃ የማይታይ መንፈስ ቅዱስ ልጅነትን ማሰጠቱ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መተባበሩ ምስጢር ያሰኘዋል።።
- እንኳንስ የጥምቀት መወለድ - የሥጋ መወለድም ረቂቅ ነው
- ከእናትና አባት ተራክቦ የሕያዊት ነፍስ መገኘት ረቂቅ ነው በሥጋም ተከፍሎ(መዋለድ) መልክ የማያልቅበት አምላክ ሰውን ገጽ ሰጥቶ መፍጠሩ ድንቅ የሚያሰኝ ነው
- **በጥምቀት** :- ካህኑ ውኃውን በብርት አድርጎ **"አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ "** ብሎ በጸለየበት ጊዜ ያ ውኃ ውኃነቱን ሳይተው ነገር ግን ማየ ገቦ (የክርስቶስ የጎኑ ውኃ) ይሆናል (ዮሐ19...)

- **ዮሐ3፡1-12** “ ኢየሱስም መልሶ። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።
4 ኒቆዲሞስም። ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው።
5 ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።
6 ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።
7 ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ።
8 ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።
9 ኒቆዲሞስ መልሶ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው።
10 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን?
11 እውነት እውነት እልሃለሁ፥ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን፥ ምስክራችንንም አትቀበሉትም።
12 ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? “

ስንጠመቅ - ከጌታችን ጎን እንወለዳለን

- ቅ/ያሬድ "ለቤ/ክ በደሙ ቀደሳ ወበማይ ዘውጎዘ እምገቦሁ አጥመቃ በዕለተ ሰንበት እምግብርናት አግዓዛ - ቤ/ክንን በደሙ ከሁሉ ለይቶ ቀደሳት ንጽሕት ልዕልት ብርጎት አደረጋት ከጎኑ በፈሰሰው ውኃም አጠመቃት በዕለተ ሰንበትም ከተገሸነት አወጣት"

- ቅ/ዮሐ.አፈ ወርቅ (ዮሐ19 በተረጎመበት)

"ጌታችን በመስቀል ላይ ጎኑን በተወጋ ጊዜ ደምና ውኃ መፍሰሳቸው አጋጣሚ ሳይሆን የቤተክርስቲያን ልደት ነው ውኃው የጥምቀት ደሙም የጌታችን ሥጋና ደም ተብሎ የዘላለም ሕይወት የሚገኝበት ምሥጢር ብሥራት ነው"

- የእስክንድርያ አባቶች "ስንጠመቅ እንለወጣለን ስንለወጥ ልጆች እንሆናለን ልጆች ስንሆን ደግሞ ወራሾች እንሆናለን "(The History and development of Deification in the christian Tradition ,(michael J christensen) 2007,25
- ቅ/ቄርሎስ ዘእስክ "ወበሞተ ዚአሁ ተጠመቅነ- በእርሱ ሞት ተጠመቅን" ሃይ.አበው

ቁርባን ምስጢር የተባለው

- ኅብስቱ ተለውጦ(ተቀድሶ) ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደሙ ተለውጦ(ተቀድሶ) ደመ ወልደ እግዚአብሔር ሆኖ አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም በመሆን የምንቀበለው በመሆኑ ምስጢር ተባለ
- የሚለወጥበት አለመታወቁ- **ኅቡዕ** አሰኝቶታል
- (በፍሬ ቅዳሴ መካከል፤ ሀበረ ንህበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ) ሲልም የሚሉ አሉ
- **ዮሐ 6፡51-71** “ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። እንግዲህ አይሁድ። ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ። ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።
- 60 ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ። ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል? አሉ።

የቁርባኑ ምስጢር ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል የሚያደርገን ደመ ማኅተም ነው- ቅ/ኤፍሬም

- Blessed be the merciful one

Who saw the sword beside paradise

Baring the way to the tree of life ,

He came ande took to himself a body

Which was wounded so that

By the opening of his side

ኅኑን በጦር ተወግቶ የገነትን በር ፤ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ለከፈተልን መሃሪው ምስጋና ይሁን

የተጎዳውን ሥጋ/ሰውነት ገንዘቡ ለማድረግ መጣ

በተወጋው ኅኑም የገነትን መንገድ ከፈተው

/St.ephrem,commentary on Diatessaron,XXI,10/

ትንሣኤ ሙታን ምስጢር መባሉ

- ሰው ከሞተ በኋላ በቀደመ ሥጋችን በቀደመ ነፍሳትን በፍርድ ቀን ከሞት የምንነሳበት የሚፈርሰው የማይፈርበት የሚበሰብሰው የማይበሰብስበት ሆኖ ወንድ የ30 ሴት የ15 ዓመት በመሆን መንግስተ ሰማያትን እንወርሳለን ማለት ምስጢር ነው::
- እንደምንነሳ ርስቱንም እንደሚያወርደንም እናምናለን ነገር ግን መርምረን አንደርስበትም
- **1ኛቆሮ15፡16** **“ሙታን የማይነሱ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሳም ክርስቶስም ካልተነሳ እምነታችሁ ከንቱ ናት እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋል...አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቱአል”**

ትንሣኤ ሙታንን ምስጢር የሚያሰኙት ነገሮች

- 1ኛ.ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱ በራሱና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሞትን ድል አርጎ መነሳቱ
- 2ኛ.ከትንሣኤም በኋላ ተዋሕዶው አለመለወጡ
- 3ኛ.በክርስቶስ በኩርነት እኛም በመጨረሻው መነሳታችን
- 4ኛ.የሚበሰብሰው የማይበሰብስ ሆኖ መነሳቱ
- 5ኛ.የ30ና የ15 ሆነን መነሳታችን
- 6ኛ.የጌታችን አመጣጡ ጎቡዕ መሆኑ
- 7ኛ.የምንናፍቃት መንግስተ ሰማያት ለሰው ልጆች መከፈትዋ

አምስቱ አዕማደ ምስጢራት ለምን 5ት ሆኑ

- 1ኛ.አራቱ ባሕርያተ ሥጋ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስ ላለው ሰው ልጅ ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ለማስረዳት ነው
- 2ኛ.ምሳሌነት ስላለው ነው
- **የዳዊት አምስቱ ጠጠሮች**(1ኛ ሳሙ 17:40)፡- **ዳዊት - የሊቃውንት ፣ ጎልያድ - የመናፍቃን ፣ አምስቱ ድንጋይ - የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ፣ ኮሮጆ - የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናቸው።።**
- ዳዊት ከአምስቱ ጠጠር በአንዱ ጎልያድን እንደገደለው ሊቃውንትም በዘመናቸው የሚነሡትን መናፍቃን እንደምንፍቅናቸው ከአምስቱ አዕማደ ምስጢር እየጠቀሱ ለመርታታቸው ምሳሌ ነው።።
- አንድም፡- ዳዊት- የጌታ ፣ ጎልያድ - የዲያቢሎስ ፣ አምስቱ ድንጋይ - የአምስቱ አዕማደ ምስጢር
- ዳዊት ከአምስቱ ጠጠር በአንዱ ጎልያድን እንደገደለው ጌታም ዲያቢሎስን ከ5ቱ ምስጢራት አንዱ በሆነው በምስጢረ ሥጋዌ ድል በማድረግ ከምዕመናን ልቡና ለማጥፋቱ ምሳሌ ነው።።

- **አምስቱ እርከኖች (ዮሐ 5፡2)**፡- አምስቱ እርከኖች - የአምስቱ አዕማደ ምስጢራት ፣ አምስቱ ድውያን - የአምስቱ ጾታ ምዕመን (እንስት፣ ወራዙት፣ አእሩግ፣ ካህናት፣ መነኮሳት) ምሳሌ ናቸው::
- እነዚህ ድውያን ለመዳን በ5ቱ እርከኖች ላይ እንደሚቆዩ፣ አምስቱ አዕማደ ምስጢርንም አምኖ የሚጸና ድኅነትን ለማግኘቱ ምሳሌ ነው::7
- **አምስቱ ሕብስት** (ዮሐ 6፡9)፡- አምስቱ ሕብስት - የአምስቱ አዕማደ ምስጢር፣ ሁለቱ ዓሳ- የፍቅረ እግዚአብሔርና የፍቅረ ቢጽ ምሳሌ ነው::
- አምስቱን ሕብስት ከሁለቱ ዓሳ ጋር አብዝቶ እንደመገባቸው አምስቱ አዕማደ ምስጢርን ፍቅረ እግዚአብሔርና ከፍቅረ ቢጽ ጋር ገንዘብ አድርገው ይማሩታልና ነው::
- **መሰንቆ፡-** መሰንቆ አንዱ ክር በአምስት ጣት እንደሚቃኝ አንድ ሃይማኖት በአምስቱ አዕማደ ምስጢር ለመቃኘቷ ምሳሌ ነው::
-

